# “ መልካም አስተዳደር የልማት መሰረት ነው”

በመልካም አስተዳደር መስፈን እና አለመስፈን ተጠቃሚው ወይም ተጎጂው ህዝብ ነው። መልካም አስተዳደር የሰፈነበት ሥርአት ሲኖር ህዝብ የተሟላ የፍትህና የማህበራዊ አገልግሎት፣ የልማትም ተጠቃሚ ይሆናል። በተቃራኒው መልካም አስተዳደር ሲጓደል ፍትህ ይዛነፋል፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች ይጓደላሉ፣ ልማት ይጎተታል። በመሆኑም መልካም አስተዳደርን የማስፈን ተግባር ቀዳሚ ባለቤቱ ህዝብ ነው። መንግስትን የመሞገት ባህል ያለው ህዝብ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን በማደረግ ረገድ ትልቅ ድርሻ አለው። ሞጋች ህዝብ መንግስት እና አመራሮቹ መልካም አስተዳደርን ከማሰፈን ውጭ አማራጭ እንዳይኖራቸው ያደርጋል። መንግስቱን የሚሞግት ህዝብ እንዲፈጠር ግን በ“**መልካም አስተዳደር**” ምንነት ላይ የተሟላ ግንዛቤ ያለው ህዝብ መኖር የግድ ይላል። ስለሆነም የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት መልካም አስተዳደርን በተመለከተ ይህንን ብሮሸር አዘጋጅቷል።

**የመልካም አስተዳደር ፅንሰ ሀሳብ አመጣጥና ምንነት** ፡- የመልካም አስተዳደር ጽንሰ ሀሳብ ብቅ ያለው በ1980ዎቹ በዓለም አቀፍ ፋይናንስ ተቋማት (IFI’s) አማካይነት ነው።

- የአለም ባንክ( World Bank )
- የአለም የገንዘብ ድርጅት( IMF )
- የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅ( UNDP

**ለጽንሰ ሀሳቡ መከሰት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች**

1. ተቋማቱ ለታዳጊ አገራት( developing countries )ሲሰጡ የነበረው የፋይናንስ ድጋፍ ውጤታማ አለመሆን ነው፡

ለዚህ ዋናው ምክንያት፡-የተቋማት/ institutions/ ፣የመርሆዎች /principles / እና የአደረጃጀት / structures / በአጠቃላይ "**የአስተዳደር**" በኋላም በደንብ ሲፈተሸ "**የመልካም አስተዳደር**" አለመኖር መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ 1989“Sub-Saharan Africa —from Crisis to Sustainable Growth” በሚል ርዕስ የተጠናው የዓለም ባንክ ጥናት በአገራቱ፡-ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነት፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ያልሆነ የፐብሊክ ሰርቪስ፣ ተአማኒነት የሌለው የፍትህ ስርዓት፣ ለህዝብ ተጠያቂ ያልሆነ አስተዳደራዊ ስርዓት፣ ለውጤት ማጣት ምክንያት መሆኑን በመለየት ይህን ችግር ለመፍታት መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ አስቀምጧል፡፡

**በዓለም የተከሰተው ያልተገመተ የፖለቲካ ለውጥ በ1989 የበርሊን ግንብ** መፍረስ፣ **በ1989 የሶቪዬት** ህብረት መፈረካከስና ይህን ተከትሎ የተከሰተው **የምስራቅ ጎራ**(Eastern Block) የኢኮኖሚና የፖለቲካ አንድነት መክሰ **( ኒኮልማልዶናንዶ፣2010)**

ለውጡን ተከትሎ በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የመንግስት ድርሻ ምን መሆን አለበት በሚለው ዙሪያ ተከታታይ ውይይቶች ተካሂደዋል። በዚህም መልካም አስተዳደር የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ትኩረት እያገኘና እያደገ መምጣቱን የተለያዩ ጽሁፎች ያስረዳሉ፣

**ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የመልካም አስተዳደር መርሆዎች ተደርገው የተወሰዱ**




እነዚህ **ስምንቱም** መርሆዎች እርስ በርሳቸው **የተቆራኙና** አንዱ ያለአንዱ ትርጉም የማይኖራቸው **መሰረተ ሀሳቦች** ናቸው፡፡ በመሆኑም መልካም አስተዳደርን በተሟላ ሁኔታ ለማስፈን ሁሉም መርሆዎች እኩል ትኩረት ተሰጥቷቸው እየተሳሰሩና እየተመጋገቡ ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡፡

ከዚህ ባሻገር መርሆዎቹ ለብቻቸው የሚሳኩ ሳይሆን **ከዴሞክራሲያዊ** ስርዓት ግንባታና **ከልማት** ጋር ተያይዘው የሚፈጸሙ ናቸው፡፡ **በአጠቃላይ በአገራችን እየተተገበሩ ያሉ መርሆዎች፡-**

◊ የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘቡ፣

◊ የገጠሩንና የከተማውን ህዝብ ተሳታፊነትና ፍትሀዊ ተጠቃሚነት

የሚያረጋግጡ፣ድህነትን ለመቀነስ፣ ልማትን ለማረጋገጥና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታን ለማፋጠን፣ የጎላ ድርሻ ያላቸውን የመልካም አስተዳደር መርሆዎችን በመምረጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

**መልካም ያልሆነ አስተዳደር ምንነት፣ መገለጫ ፣ባህሪያትና የሚያስከትለው አደጋ**

መልካም ያልሆነ አስተዳደር የመልካም አስተዳደር ተቀራኒውን ገጽታ የያዘ ሲሆን፡- ሙስናን የሰብዓዊ መብት ጥሰትን፣ ግልጽነትና የተጠያቂነት አሰራር መጓደልን፣ ፈጣን ምላሽ አለመስጠትን፣ የመንግስትንና የህዝብን ሀብት በቁጠባና በውጤታማነት ስራ ላይ ማዋል አለመቻልን እና የህግ የበላይነት አሰራር አለመስፈንን የሚያጠቃልል ነው (ዋኤል ኦምራን፡2013)መልካም ያልሆነ አስተዳደር መገለጫዎች ውስጥ አንዱ ሙስናና ብልሹ አሰራር ነው፡፡ በብዙዎች ዘንድ የሚታወቀውና በጣም ቀላሉ የሙስና ትርጉም የመንግስትን/የህዝብን ሀብት ለግል ጥቅም ማዋል ነው **(የዓለም ባንክ፣ 2012) ፡፡** ለሙስና መንሰራፋትና መባባስ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ ተግባራት መካከል የተጠያቂነት አሰራር አለመኖር፣ ውጤታማና ቀልጣፋ ያልሆነ ተቋማዊ አሰራርና አደረጃጀት፣ የህጐች ደንቦችና መመሪያዎች ግልጽ አለመሆን---ወዘተ ነው፡፡ **እንደ ራቸል (2012)** አባባል ሙስና በግልጽነት መጓደል የሚከሰት ሲሆን በአንድ አገር አለመረጋጋትንና ያልተጠበቀ አስተዳደራዊ ቀውስን የሚያስከትል አደገኛ ተግባር ነው፡፡

በብዙዎች ዘንድ የሚታወቀውና በጣም ቀላሉ የሙስና ትርጉም የመንግስትን/የህዝብን ሀብት ለግል ጥቅም ማዋል ነው (የዓለም ባንክ፣ 2012) ፡፡ ለሙስና መንሰራፋትና መባባስ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ ተግባራት መካከል የተጠያቂነት አሰራር አለመኖር፣ ውጤታማና ቀልጣፋ ያልሆነ ተቋማዊ አሰራርና አደረጃጀት፣ የህጐች ደንቦችና መመሪያዎች ግልጽ አለመሆን---ወዘተ ነው፡፡ እንደ ራቸል (2012) አባባል ሙስና በግልጽነት መጓደል የሚከሰት ሲሆን በአንድ አገር አለመረጋጋትንና ያልተጠበቀ አስተዳደራዊ ቀውስን የሚያስከትል አደገኛ ተግባር ነው፡፡የግልጽነትና የተጠያቂነት አሰራር መጓደል ሌላው የመልካም ያልሆነ አስተዳደር ባህርይ ነው፡፡የግልጽነትና የተጠያቂነትአሰራር አለመኖር ህግና ደንብን የተከተለ አሰራር አለመኖር መሪዎች ወይም በስልጣን ላይ ያሉ አካላት ያሻቸውን የማድረግና የመወሰን ነጻነት ይኖራቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዜጎች ከመንግስት አጀንዳ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን የማግኘት መብት ስለሚነፈጉ ሙስናው እየሰፋ ይሄዳል፡፡

**የመልካም አስተዳደር ችግር የሚያስከትለው አደጋ**

**የኪራይ ሰብሳቢነትን አሰራር ያሰፍናል**፡- የኪራይ ሰብሳቢነት በሰፈነበት አሰራር፡-የአገልግሎት አሰጣጥ ስርአቱ የብዙሀኑን ፍላጎትና ጥቅም ማዕከል ያደረገ ሳይሆን የጥቂት ኪራይ ሰብሳቢዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ነው፡፡በመሆኑም በስርአቱ የህግ የበላይነት ሳይሆን የሰው ፍላጎት የበላይነት የሰፈነበት ይሆናል፡፡የህግ የበላይነት ባልሰፈነበት ሁኔታ የመልካም አስተዳደር ሊሰፍን አይችልም፣ እንዲሁም ኪራይ ሰብሳቢነት በሰፈነበት ስርአት ውስጥ መልካም አስተዳደር ሊኖር አይችልም፡፡የተጀመረውን ፈጣን አገራዊ የልማት እንቅስቃሴ ለማሳካት እንቅፋት ይሆናል፣

ኢ-ፍትሀዊ የሆነ የሀብት ክፍፍልን ያስከትላል (ዜጎችከመንግስት የሚጠብቁትን አገልግሎት በሚፈልጉት መልክ እንዳያገኙ እና ፍትሐዊ የሆነ አሰራር እንዳይሰፍን ያደርጋል) የህዝብና የመንግስት ሀብት ያለአግባብ እንዲባክን ያደርጋል የግለሰቦች ፈላጭ ቆራጭነት ስርዓት እንዲሰፍን ያደርጋል፣የሕዳሴ ጉዞን ያደናቅፋል ፡፡

**ህዝብ በመንግስት ላይ ያለውን እምነት ይሸረሽራል፣** የየትኛውም መንግስት ስርአት ተረጋግቶ ሊኖርየ ሚችለው ህዝቡ በመንግስት ላይ እምነት ሲኖረው ነው፡፡ የህዝብ አመኔታ በሌለበት ወይም ዝቅተኛ በሆነበት ስርአት የትኛውንም እቅድ ከግብ ለማድረስ አዳጋች ነው፡፡ ዜጎችም ያላቸውን አቅም ሁሉ በመጠቀም የመንግስትን ፖሊሲና ስትራቴጂን መሬት ለማውረድ ወይም ለመተግበር አይተጉምበመሆኑም ማንኛውም የልማት እቅድ ከግብ ሳይደርስ ይቀራል፡፡ በመሆኑም የመልካም አስተዳደር ስረአት እንደሰፍን ሁላችንም የድርሻችንን እንወጣ መልክታችን ነው ፡፡

**“ መልካም አስተዳደር- የፈተናዎቻችን ሁሉ ቁንጮ ”**

**የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት**